# የማን መብት?

አብርሃም በየነ

አንድ ትውልድ መትረው በጅምላ የፈጁ
የወጣት አበባ አፈር ውስጥ ያስረጁ

የምሁር አዝመራ አጭዶው የወቁ
የሰውን ስብዕና በስዬል የፋቁ

በፋሽሽት ህዳሴ መግደል የተካኑ
ማህፀን አድርቀው ወላድ ያመከኑ፤

ከናዚ ጭካኔ በልቅና ገዝፈው
በግፍ አገዳደል የደም ጎርፍ አጉርፈው፤

በንፁህ ደም መስኖ ሞት ያለመለሙ
በሰው ደም ዋኝተው ቀይ የተቀለሙ፤

በራፍ ላይ ለጣሉት ተበሳስቶ አካሉ
ለሞተበት ጥይት ዋጋ ያስከፈሉ፤

መራሩ ሀዘኗ አንጀቷን አርዶ አርዶ
ዕብድና ሙር አርጓት የልጇ ሞት መርዶ፤

በለቅሶ ዳስ ድንኳን፤ ባዘን ቤት ዋይታ
ተነሽና ዝፈኝ ውረጅ ያሉ አስክስታ፤

የልጇ ገዳዮች የግፍ ግፍ አንዲሉ
ሀዘኗን ባፈሙዝ ሠርጓን ያስመሰሉ
ደርግና ኢሠፓ ኮሎኔል መንግሥቱ
የሟች ነው የገዳይ?
በደም የመነገድ፤ የማን ነው መብቱ?

ጥር 2004